አልላሁመ ቂኒ ዐዛበከ የውመ ተጅመዑ አው ተብዐሡ ዒባደክ"» ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ባሮችህን በምትሰበስብበት ወይም በምትቀሰቅስበት ቀን ከቅጣትህ ጠብቀኝ።" ማለት ነው።

ሑዘይፋህ ቢን አል'የማን -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላችውና- እንዳስተላለፉት: «ነቢዩ -የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- መተኛት የፈለጉ ጊዜ እጃቸውን ጭንቅላታቸው ስር ያኖሩ ነበር። ቀጥለውም እንዲህ ይሉ ነበር: "አልላሁመ ቂኒ ዐዛበከ የውመ ተጅመዑ አው ተብዐሡ ዒባደክ"» ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ባሮችህን በምትሰበስብበት ወይም በምትቀሰቅስበት ቀን ከቅጣትህ ጠብቀኝ።"
ማለት ነው።
[ሶሒሕ ነው።] [ቲርሚዚ ዘግበውታል።]

ነቢዩ -የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና- ለመተኛት ስፍራቸውን ሲይዙ ቀኝ እጃቸውን ይንተራሱና ቀኝ ጉንጫቸውን ቀኝ እጃቸው ላይ በማኖር እንዲህ ይሉ ነበር: "አልላሁመ ቂኒ ዐዛበክ" አላህ ሆይ! ጌታዬ ቅጣትህን ጠብቀኝ። "የውመ ተጅመዑ አው ተብዐሡ ዒባደክ" የሒሳብ ቀን የትንሳኤ ቀን ማለት ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/6167